# የሙስና ፅንሰ ሃሳብ

በአቶ መለሰ

## 1.1. የሙስና ትርጉም

### ሀ. አክስፎርድ ዲክሽነሪ (Oxford Dictionary)

- አደራን አለመጠበቅ፣ እምነት ማጉደል፣
- በጉቦ፣ በምልጃና በአድሎ፣ ሐቅን፣ ውሳኔን ወይም ፍትህን ማዛባት፣

### ለ. ካቶ፡- (Kato, 1996)

- ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል፣ ሥርዓቶችን፣ ደንቦችን፣ ህጐችንና መርሆዎችን መጣስ ነው፡፡

### ሐ. የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ 1993

- የመንግስትን ሥራ ሥነ ምግባራዊና ህጋዊ መሠረት ባለው መመሪያና ደንብ ላይ ተመርኩዞ አለመስራት፡፡

### መ. Transparency International

- በመንግስትና በህዝብ የተሰጠን ሥልጣንና ኃላፊነት ለግል ጥቅም፣ ወይም ሌላን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል በስልጣን አለአግባብ መገልገል ነው፡፡

> ሙስና ህግና ሥርዓትን ተከትሎ ከማስራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ህግና ሥርዓትን በመጣስ የመንግስትና የህዝብ ሃብትና ንብረትን ማስረቅ፣ መዝረፍ፣ ማጭበርበር እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ በጐሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትሥሥር በመመርኮዝ ፍትህን አያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላውን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም መጉዳት ነው፡፡

- ቂም በቀል፣
- ጥላቻ
- ግብታዊነት

- ጀብደኝነትና
- ጊዜያዊ ስሜት ነው፡፡

ሙስና ግን ከስሜት ውጭ በረቀቀ ስልትና እቅድ /በንቃት/ የሚፈፀም ነው፡፡

## ለ. ለጉዳዩ ባለቤት ነኝ ባይ አለመኖሩ

- ሌሎች ወንጀሎች የሚያደርሱት ጉዳት በአንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ላይ ሲሆን ተበዳይ ጉዳዩን ቶሎ ወደ ህግ ያቀርባል፡፡ በተቃራኒው የሙስና ወንጀል በሃገርና በህዝብ ላይ የሚፈፀም በመሆኑ ተጐጂ ነኝ ብሎ በባለቤትነት ብዙ ለህግ የሚያቀርብ የለም፡፡

## ሐ. የፈፃሚዎች ማንነትና ከምርመራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ለማጥቃት መቻላቸው፡፡

- አብዛኛውን ጊዜ ነባር ወንጀሎች /ግድያ፣ዝርፊያ፣ድብደባ፣አሥገድዶ መድፈር፣ወዘተ…/ የሚፈጸሙት በአብዛኛው በትምህርት ባልገፉና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ባሉ ሰዎች ሲሆን በተቃራኒው የሙስና ወንጀል ፈፃሚዎች በተማሩ፣ ስልጣን ባላቸውና ሃብት ባላቸው ሰዎች ሲሆን በረቀቀ ስልትና ማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ ሁሉ በዕቅድ በማከናወን ነው፡፡

## መ. በህዝቡ ዘንድ እንደነውር አለመታየቱና ሙስናን ለመዋጋት የተሰማሩትን ሰዎች ማሸማቀቁ

- ህዝቡ ግድያና ሌሎች የተለመዱ ወንጀሎችን በግልፅ ሲያወግዝና ሲያጋልጥ ይታያል በአንፃሩ ሙስና የፈፀመውን ሰው እንደ ብልህና ቀልጣፋ በመውሰድ ሲያበረታታ በሌላ በኩል ደግሞ ሙስናን ለማጋለጥ የተነሱ ሰዎችን እንደ ሰባቂ፣ ምቀኛና አቃጣሪ በመፈረጅ ከማህበሩ ሲያገል ይታያል፡፡

## 1.3. የሙስና ዓይነቶችና መጋለጫቸው

## ሀ. ዝቅተኛ ሙስና (Petty Corruption)

- ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ሲሆን በየደረጃው በሚገኙ፡-
  - ✓ የመንግስት ሠራተኞች፣
  - ✓ ባለስልጣኖችና በአገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች የሚፈፀም ነው፡፡

## ለ. ከፍተኛ ሙስና (Grand Corruption)

- መጠነ ሰፊ የሆነ የመንግስት ሃብትና ንብረት፣በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣኖችና በከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚዘረፍበትና የሚመዘበርበት ነው፡፡

  **<u>ምሳሌ</u>**፡- የፕሮጀክት ውሎች፣

  ባንኮች፣

  የገቢ ሰብሳቢዎች

  መሰረተ ልማት ላይ የተሰማሩ መ/ቤቶች፣ /ት/ቤት፣ መንገድ፣ ውሃ፣ ቴሌ፣ ሙብራት፣ ጤና ወዘተ/

## ሐ. <u>ፖለቲካዊ ሙስና</u>

የአንድን ማህበረሰብ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕሴቶችና ልማዶችን በመጣስ ይፈፀማል፡፡

## <u>መግለጫዎቹ</u>

i. በምርጫ ወቅት የሚፈፀም (Electoral Corruption)

ii. የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy)

iii. በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈፀም ሙስና (Corruption in legislation process)

## 1.4. <u>የሙስና መገለጫዎች</u>

## ሀ. <u>ጉቦ /እጅ መንሻ/</u>

- ህጋዊ አሰራርን ለማስቀየር የሚሰጥ ማንኛውም መደለያ ነው፡፡

  - <u>ጉቦ በሁለት ይከፈላል</u>
    - ✓ ከተገልጋይ የሚነሳና (Bribery)
    - ✓ ከአገልጋይ የሚጠየቅ (Extortion)

## ለ. <u>ምዝበራ (Embezzlement)</u>

ከመንግስትና በህዝብ በተሰጠ ስልጠንና ኃላፊነት በመቀጠም የመንግስትን ሐብትና ንብረት መዝረፍ፣ መስረቅ፣ መውሰድና ማሳወሰድ፡፡

## ሐ. <u>ማጭበርበር (Fraud)</u>

- ህጋዊ ሠነዶችን መቀየርና ሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት
- የተሳሳተ መረጃ መስጠት
- ፎርጅድ ብሮችን ማዘጋጀት

## መ. አድሎ(Nepotism and favoritism)

ይህ የሙስና ወንጀል በዝምድና፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በወዳጅነት ላይ ተመርኩዞ የሚሰራ ነው፡፡

## የአፈፃፀም መግለጫዎች

- በሥራ ቅጥር፣ በዝውውር በእድገት፣
- ለትምህርት እድል በሚደረግ ምልመላ

## 2. የሙስና ታሪካዊ ገፅታ በኢትዮጵያ

### 2.1 . በኃይለስላሴ ዘመን

በመንግስት ሹመት አሰጣጥ ላይ ሙስና ህጋዊ ማዕቀፍ ነበረው፡፡

ለምሳሌ፡- - ለወረዳ አስተዳደሪነት 3000

- ለአውራጃ አስተዳዳሪነት 5000
- ለሃገረ ገዥነት 10000 ብር ይከፈል ነበር
- የመታያ ቢሮ

### 2.2. በደርግ ዘመን

- የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሥነ ምግባር መዳከምና፣
- የመልካም ሥነ ምግባር እሴቶችና ሞራሎች መውደቅ

### 2.3. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ዘመን

- በነፃ ገበያው ምቹ ሁኔታ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትሜንት ሲሰፋፋ ሙስናም አብሮ ተስፋፍቷል
- በ1993 ዓ.ም በተደረገው ጥናት በሚከተሉት ተቋማት ሙስና እየተፈፀም እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

**i. በመሬት አመዳደብ፣**

**ii. የህዝበ ቤት አሰጣጥ፣**

**iii. ዳኞች፣**

**iV. የፍ/ቤት አሠራርና**

**v. የግብር አሰባሰብ ዘዴ**

## 3. የሙስና መንስኤዎች

### 3.1. መሠረታዊ ምክንያት (Basic Cause)

#### i. የሥነ ምግባር ዝቅጠት /መበላሸት/

ምሳሌ፡- የመስረቅና የሥግብግብነት ባህሪ መኖር፣

ሣይሰሩ በአቋራጭ የመክበርና የተደላደለ ህይወት የመኖር ፍላጐት፣

ለተለያዩ ሱሶች መጋለጥ /ቁማር፣ መጠጥ/

ግለሰቦች ከሌላው ሰው ጋር ሲወዳደሩ የሚሰማቸው የበታችነት ስሜት፣

ግለሰቦች ከህግ በላይ የመሆን ሥሜት፣

ግድ የለሽነትና የኃላፊነት ስሜት ማጣት፡፡

### 3.2. ሙስናን የሚያባብሱ ምክንያቶች (Immediate Cause)

#### i. ኢኮኖሚያዊ ምክንያት

- ድህነት፣
- ሥራ አጥነት
- ኃላቀርነት፣

#### ii. ፖለቲካዊ ምክንያት

- የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር /የዲሞክራሲ ሥርዓቶችንና ዕሴቶችን አለማክበር/
- ልዩ ልዩ ደምቦችና መመሪያዎች አለመኖር፣
- ነፃ ፍ/ቤት አለመኖር፣
- ከመጠን በላይ የተማከለ አስተዳደር፡፡

#### iii. ባህላዊና ሥነ ልቦናዊ ምክንያቶች፣

#### ሀ. ባህላዊ ልምዶች፣

- ጉዳይ እንዲፈፀም ጉቦ መስጠት
- ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል

#### ለ. ዝምድናን፣ ማህበራዊ ትስስርንና ውለታን መሠረት ማድረግ

#### iv. ተቋማዊ ምክንያቶች

- ግልፅ የሆነ መመሪያና ደምብ አለመኖር /የሥራ መመሪያና የሥነ ምግባር ደምብ/

- በተቋሙ ውስጥ ለሥራም ሆነ ለሠራተኞች ምቹ ሁኔታ አለመኖር፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት አለመኖር

# 4. ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

## 4.1. ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች

- የመንግስት በጀት በተገቢው ቦታ አለመዋል፣
- የግብር አሰባሰብ ደንበና ሥርዓት መዛባት
- ኢንቨስትሜንትን ይጐዳል /ከሃገር ውስጥና ከውጭ/
- የሥራና የሠራተኛ ምቹ ሁኔታዎች አለመኖር /ምርታማነትን መቀነስ/
- የተዛባ የሃበት ክፍፍል መፈጠር፣
- የሃገር ሃብት በጥቂቶች እጅ ይወድቃል /አብዛኛው ህዝብ በድህነትና በጐስቁልና ይሰቃያል/
- ለህዝብ የሚቀርብ የፍጆታ እቃ መጠንና ጥራት መቀነስ

በአጠቃላይ ሙስና፡- ልማት እንዲቀጭጭ፣
የአገር ኢኮኖሚ እድገት እንዲገታ፣
ኪሳራና ውድቀት እንዲስፍንና፣
ድህነት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

## 4.2. ማህበራዊ ጉዳቶች፣

- ተስፋ መቁረጥ /ፍትህ እኩልነትና የህግ የበላይነት መጥፋት/
- የሞራል ውድቀት /የሥነ ምግባር ቀውስ/
- የጥገኝነት አስተሳሰብ ማደግ፣
- ሥራ አጥነት፣
- ጐዳና ተዳዳሪነት፣
- ሴተኛ አዳሪነት፣
- ዋልጌነት /ጥፋተኝነት/፣
- ሥርዓተ አልበኝነት /የእርስ በርስ ግጭት/
- መሃይምነት እና
- አጠቃላይ የመሠረተ ልማት እጦት

## 4.3. ፖለቲካዊ ጉዳቶች፣

## ሀ. የዲሞክራሲ ሥርዓት እሴቶች መሸርሸር

- ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች፣
- የህዝብ ሉዓላዊነት፣
- የህግ የበላይነት፣
- ወቅታዊ ምርጫ፣
- የህገ መንግስት የበላይነት አለመኖር፣
- ነፃነት (secularism/ አለመኖር፣
- የብዙሃን ፖርቲ አለመኖር፣
- የብዙሃን ህግና የጥቂቶች መብት አለመከበርና
- የሥልጣን ክፍፍል እየጠፋና እየደበዘዙ መሄድ፡፡

## ለ. በዜጐች በመንግስትና በሀገር ላይ የሚከሰት ችግር

- ዜጐች በሚኖሩበት ሃገር ላይ የቤተኝነት ስሜት ማጣት፣
- በመንግስት ላይ እምነት ማጣት፣
- ህዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ መሆን
- የፖለቲካ አለመረጋጋት፣
- የሚወጡ ፖሊሲዎች ተግባራዊ አለመሆንና ብቃት ማነስ፣
- መንግስት በመንግስትነቱ መቀጠል አለመቻል፣ /በመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት/
- ከሥርዓቱ ምንም ዓይነት ጥቅም ያላገኙ ዜጐች እኩል ወይም የተሻለ ድርሻ ለማግኘት የሃይል አማራጭን በመከተል ትግል ይጀምራሉ በዚህም ምክንያት የእርስ በርስ ግጭቶች ይነሳሉ፣
- በርስበርስ ጦርነቱ ወቅትም ሙስና የበለጠ ይስፋፋል በዚህም ምክንያት ጦርነቱ ለረጅም ጊዜ ይቆያል፡፡ /ሱማሊያ፣ ላይቤሪያ፣ ኮንጐ፣ ሲራሊዮን/
- በዲሞክራሲ ሥርዓቱ ላይ ጥርጣሬ መኖርና ዜጐች ለሥርዓቱ ግምባታ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዳያደርጉ ይገታል፡፡

## 4.4. ከባቢያዊ ጉዳቶች፣

- የተፈጥሮ ሃብትን ኃላፊነት በጐደለው መልኩ ማጥፋት፣
- የተፈጥሮ ጤናማ ከባቢያዊ ዑደትን መበከል፣ /የካርቦን ልቀት፣ የኬሚከል ዝቃጭ/

## 1. የሙስና መከላከያ ስትራቴጅዎችና ስልቶች፣

### 1.1. ግልፅነትና ተጠያቂነት

### 1.1.1 ግልፅነት

- ህብረተሰቡ በመንግስት ውሳኔዎች ላይ በንቃት መሣተፍ፣
- ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድና ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማዘጋጀትና ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ማድረግ፣
- አስፈፃሚው የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ረቂቅ ህጐች ህብረተሰቡ አስቀድሞ ሊወያይባቸውና አስተያየት እንዲሰጥባቸው ማድረግ፡፡

### 1.1.2. ተጠያቂነት

- ሥራን በአግባቡ እንዲሰራ የተሰጠ አካል ተግባሩን ካላከናወነ በህግ የሚጠየቅበትና ካሳ የሚከፍልበት ነው፡፡

## 1.2. ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣኞች የሚጠበቁ ተግባራት፣

- ግልፅ የሆነ የመ/ቤቱን ራዕይ፣ ተልኮ ዓላማና ግብ ማስቀመጥ፣
- ስትራቴጅክ እቅድና ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት፣
- ውጤት ተኮር ማዘጋጀት፣
- ግልፅ የሆነ የሥራ ክፍሎች የሥራ መዘርዘር፣
- የሥነ ምግባር መርሆዎች መኖር፣